ከጎቦ ዉቃዉ ጥቅምት 23/2000
ኦርሊየንስ-ኦቶዋ-ካናዳ

# ቶኪቻው!፤ቶኪቻው!
# “ፀጋዬ ደ-ብ-ተ-ራ-ው!”
# ለድኩማን ማረቂያ አርጩሜህን ልዋሰው፤
# ለብእር-ነዳያን ላውለው!

ቶኪቻው ልበልህ፤ደብተራው
በእርግጥ መንጎል ሁሉም መንጎል ነው?
እንዲያውቅ፤መጣፍ-በብዕር
ምነው ሁሉም ባንተ?
ቢ-ሰ-ገ-ር፤ እ-ን-ዲ-ሰ-ግ-ር

ከፀሀፍት፤ደጀ-ሰላማ
የገለማ፤አክርማ. . .
አለማወቁን፤የማይሰማ
ሲዳዳው፤ፍርፉሪ ለቀማ
**ተይዞአል!. . .**
“በጫጫሪነት”-አፈላማ!።

ሲቦካ፤ሲያቦካው
ልክፍቱም አይለቀው

**“ከበሮም በሰው እጅ ያምር”**
**ሲይዙት ግን ያደናግር”**
ቢንገዳገድ፤ቢፍጨረጨር
በእጅ በእግሩ፤ቢውተረተር
ቢንገዳገድ፤ሊቆም ቢጥር
ሁሉም ብዕር ነው ወይ? ብዕር?
ያለ ሙያ መሰንቀር
የዕውር-ድንብር
**አይቀል! እንደመናገር**
እዚያው፤እዚያው፤መንቡአቸር
የዕውር-ድንብር
ያለቦታው ሲሰነቀር

በጎበ-ዉቃዉ

ተደናብሮ፤ማደናበር
ምነው እዚያ ቢል ጥንቅር!።

የገለማ፤አክርማ. . .
አለማወቁን፤የማይሰማ
በቢጤዎቹ ሆይ-ሆይታ
ትንስ-ራሱ ሰማይ ወጥታ
ዶሮ-ማታ፤ዶሮ-ማታ!
የድኩማን፤አ-ው-ታ-ታ!
በአንድ ቅኝት ሁካታ
ባዶ ስድብ፤ድንፋታ!።

ወፌ ቆመች! ወፌ ቆመች!
ነጋም፤መሸም፤ዳከረች
ያለቂዬዋ ዞራ፤ ከማጥ ተነከረች።

ዜማም የለው፤ቆርቆሮ
ሄደም-መጣም፤እዚያው ዞሮ
በአለበት ተገትሮ
ጭሮ!. . .ጭሮ. . .!ጭሮ!. . .ጭሮ!
ወይ!ተፃፈና-ተኖሮ!
አልተሻለም ከዶሮ
ጭሮ!. . .ጭሮ!. . .ጭሮ!. . .ቡአጭሮ!
እርባን የለሽ ዕንጉርጉሮ።

# አሎቶ! ላሎቶ

የመጣጥፍ ድሪቶ
እንዲያው፤እንቶ-ፈንቶ
መካሪ-የለሽ፤ተንከራቶ
አያገባው፤ገብቶ
ሊኖር የቆረጠ ከቶ
በራሱ ላይ ግብ-አግብቶ!
በራሱ ላይ ተዘባብቶ
ፍልቃቂት፤ባዘቶ
ወይ-አለቱ!፤ወይ-አሎቶ!

ቀለሙን የጨረሰ. . .
. . .የገነፈለ “እስክሪብቶ” ።

ለባንድነት-ያነጠነጠ
ያለ-ዐቅሙ፤ተንፈራገጠ
ፉት-ቢሉት፤ተጨለጠ
ሳ-ያ-ብ-ጥ-የፈረጠ
ሳ-ይ-ሞ-ቀ-ው-የቀለጠ
ጎ-ር-ን-ቶ-የሰነፈጠ
ሳ-ይ-በ-ስ-ል-የቆመጠጠ
በ-ጨ-ቅ-ላ-ነ-ቱ-ያረጠ
ሳ-ይ-ገ-ባ-ው፤አንቐለጠ
ከጅምሩም-ያረጠ
ለዛውን-የሙአጠጠ
ያዙት፤ልቀቁት. . .
ተነሳ፤ፈረጠ!
እንደገናም፤ፈረጠ!።

እንደው. . .
ማን? ብዬ ልጥራህ!
ባዶ ቅል፤ራስ የለህ
ከወናፍም ወናፍ ነህ
ምንም የራስህ የሌለህ
የማን ነገረ-ፈጅ ነህ?
ላንዴም! ለሁሌም! የሂ ይብቃህ
የጎለደፈ ብርዕህ ፤ይግባ ከብብትህ!
ጉአደኛም፤ጎረቤት አይይብህ



ከበ-ወ.ቃ ወ.

ብትማስን ይሻልሀል. . .
ላንዲትዋ፤ምስኪን ነፍስህ
አትዋል ያለመንደርህ
ወይስ ከደርግ-ከወያኔ. . .
ኖሮ እንደሁ የዘር-ግንድህ?
የሚያንጠራራ፤ጂኒህ
እግዚኦ ብለናል፤ይማርህ
አነኑ ብለናል ይብቃህ

**ይሄ የፅሁፍ አርጩሜ አንተን እና ቢጤዎችህን ቆም ብላችሁ እራሳችሁን እንድትጠይቁ “ዱራ-ገዎቹም” ከማፈሪያነታቸው እንዲታቀቡ ማርቂያ ይሆን ዘንድ ነፃ-መርገመ-በረከት ነው።**

አርጩሜውን እንዲረዱ በቅጡ
የፅጋዬን አንደበት በሚከተለው ያድምጡ
(www.debteraw.com) ግንባርህን አሳያቸው

**“የፅህፈት-ነዳያን” ምህረቱን ያብዛላቹህ**

**ከ ዕድምተኞቹ ጋር ቸር ይግጠመን**